Waggaa 9ffaa ........................ Lak. 12
፱ኛ ዓመት ........................ ቁጥር ፲፪
9th year ........................ No. 12

Finfinnee, Gurraandhala 18/1995
ፊንፊኔ፣ የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፭

# MAGALATA OROMIYAA

# መገለተ ኦሮሚያ

# MEGELETA OROMIA

| | | |
|---|---|---|
| Gatiin Tokkoo .................... 17·89<br>ያንዱ ዋጋ .................... "<br>Unit Price .................... " | Too'annaa Caffee Mootummaa Naannoo Oromiyaatiin Kan Bahe<br>በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ | Lakk. S. Poostaa .................... 101769<br>የፖ·ሣ·ቁጥር .................... "<br>P.O.Box .................... " |

QABEENTAA

Mootummaa Naannoo Oromiyaatti Dambii Aangoofi hojii Manneen Maree Bulchiinsa Aanaafi Gandaa tartiibaan Murteessuuf bahe lakk. 30/1995 .................... fuula 1

ማውጫ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የወረዳ እና የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፴/፲፱፻፺፭ .................... ገጽ ፩

## *Dambii Lakkoofsa 30/1995*

## *Mootummaa Naannoo Oromiyaatti Dambii Aangoofi hojii Manneen Maree Bulchiinsa Aanaafi Gandaa tartiibaan murteessuuf bahe*

Sirna Bulchiinsaa Aangoofi hojii gadi buusuu (decentralization) hojiirra oolchuuf, ijaarsa sirna dimokiraasii haala amansiisaa ta'een fiixaan baasuufi hirmaannaa dammaqaa ummataa mirkaneessuuf humna raawwachiisummaa Aangoo sadarkaa gadi aanaa jabeessuun barbaachisaa ta'ee waan argameef;

Bulchiinsa gaarii mirkaneessuuf; iftoomaafi itti gaafatamummaa dhugoomsuuf; tarsiimoowwaniifi sagantaalee misooma badiyyaa, sagantaa wabii nyaataafi tarsiimoo hiyyummaa hir'isuu, akkasumas misooma ariifachiisaa waliigalaa mirkaneessuufi hojiirra oolchuuf aangoo fi hojii manneen Maree Aanaafi Gandaa guutuu ummataa sosochoosuu dandeessisu tartiibaan murteessuun barbaachisaa ta'ee waan argameef;

Akkaataa Labsii gurmaawina qaamoota raawwachiiftuu Mootummaa Naannichaa fooyyessuufi Aangoofi hojii isaanii irra deebi,uudhaan murteessuuf bahe labsii lakkoofsa 50/1994 keewwata 65 (1)tti Danbiin kanatti aanu baheera.

### *BOQONNAA TOKKO*
### *Tumaatoota Waliigalaa*
### *Kutaa Tokko*

1. *Mata duree gabaabaa*

Dambiin kun Mootummaa Naannoo Oromiyaatti Dambii Aangoofi hojii Manneen Maree Bulchiinsa Aanaafi Gandaa tartiibaan murteessuuf bahe lakkoofsa 30/1995 jedhamee waamamuu ni danda'a.

## ደንብ ቁጥር ፴/፲፱፻፺፭

## በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የወረዳ እና የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤቶች ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር ለመወሰን የወጣ ደንብ

ያልተማከለ አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ፤ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውን በአስተማማኝ ከዳር ለማድረስና የነቃ የሕዝብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የዝቅተኛውን የሥልጣን እርከን የማስፈጸም አቅም ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ፣ የገጠር ልማት እስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን፣ የምግብ ዋስትናውን ፕሮግራምና የድህነት ቅነሳውን እስትራቴጂ እንዲሁም አጠቃላይ ፈጣን ዕድገት ለማረጋገጥና ተግባራዊ ለማድረግ ምልዓተ ሕዝቡን ለማነቃነቅ የሚያስችል የወረዳና የቀበሌን አስተዳደር ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልሉን መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ለማሻሻልና ሥልጣናቸውንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፶/፲፱፻፺፬ በአንቀጽ ፷፭ (፩) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ደንብ ወጥቷል።

### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች
### ክፍል አንድ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የወረዳ እና የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፴/፲፱፻፺፭ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

(i) Aadaafi Afaan ummatichaa akka dagaagu ni godha;

(j) Ispoortiin aadaa ummataa akka ta'uufi iddoowwan oolmaya ispoortii akka babal'atan ni godha.

(k) Qaamooleen hawaasa Aanichaa adda addaa waldaalee hojii gamtaatiin akka gurmaawan ni godha. Waldaalee hojii gamtaa gurmaawaniifis deggersa barbaachisaa ni kenna;

(l) Hawwattoonni Tuurizmii Aanichaa akka beekamaniifi hirmaannaa ummataatiin hojiirra akka oolan ni godha.

(m) Ummaticha hojiiwwan misoomaatiif kakaasuudhaan karaa dimokiraatawaa ta'een akka hirmaatu ni godha.

(n) Waa'ee raawwannaa hojii isaa Mana Maree Aanichaatiifi Bulchaa Godinaatiif yeroo yeroodhaan gabaasa ni dhiheessa.

(o) Karoora Aanaa Gandaaf kennuu, karoora Gandaa tokko tokkoon ilaaluufi raawwannaasaa dhiheenyaan hordofuu.

(p) Walgeeddaruumsi muuxaannoo hoggantoota Gandaa sagantaa beekameen raawwatamu akka jiraatuufi tokko kan biroorraa akka baratu gochuu, kuniis naannoo ummata qindeessuutti, hojiiwwan misoomaa hojjechiisuutti, rakkoowwan bulchiinsaa hiikuutti ta'uutu irra jiraata,

(q) Hoggantoonni Gandaa labsoota, seerootaafi qajeelfamoota biyyattiifi Naannichaa bu'a qabeeyyii ta'anirratti hubannoo akka qabaatan ogeessoota qapheessuudhaan mata dureewwan adda addaarratti mari'achiisuutu irra jiraata;

(r) Dandeettiin ummaticha haqaan tajaajiluu isaanii akka cimuufi humni malaammaltummarratti gara kuteenyaan qabsaa'uuf isaan dandeessisu akka uumamuuf seeminaaroota gaggabaabaa ogeessootaan qopheessudhaan kennuu,

(s) Manni Maree Bulchiinsa Aanichaa hir'inoota isaa gamaaggama tarkaanfiiwwan sirreessa yeroo yeroodhaan fudhachuu dabalatee miseensoonni hunduu hogganummaafi itti gaafatamummaan hojjechuun isaanii akka dagaaguufi gahuumsi raawwannaa hojii hojjechuun isaanii akka guddatu ogeessoota Aanaalee keessa jiraniin, yeroo tokko tokkoos Naannicharraa affeerraa seeminaaroota guyyaa guyyaa kennuudhaan hojiin cimsuufi gahuumsa isaanii ol guddisuu karooraan qabamee hojiirra ooluu qaba,

(t) Hojiiwwan Mana Maree Aanichaa fi Mana Maree Bulchiinsa Aanichaatiin kennamaniif biroo ni raawwata.

### *KUTAA AFUR*
### *Aangoofi hojii Miseensoota Mana Maree Bulchiinsa Aanaa*

7. *Aangoofi hojii Dura Taa'aa Bulchiinsa Aanaa*

Dura Taa'aa Bulchiinsa Aanaa itti waamamnisaa Mana Maree Aanichaatiifi Bulchaa Godinaatiif tahee, aangoofi hojiiwwan kanatti aanaan ni qabaata:-

(a) Hojiiwwan Aanichatti raawwataman, Mana Maree Bulchiinsaatiin raggaasifamaniifi qaamoota ol'aanoorraa kennaman walitti qindeessee ni hoggana, ni hordofa, ni raawwachiisa.

(b) Mana Maree Aanichaa ni gurmeessa, ni hoggana,

(c) Aanicha keessatti imaammatoonni, seeroonni, qajeelfamoonni, karooronniifi sagantaaleen Mootummaa sirriitti hojiirra ooluu isaanii ni mirkaneessa.



ቀ) የሕዝቡ ባሕልና ቋንቋ እንዲበለፅግ ያደርጋል።

በ) ስፖርት የሕዝቡ ባህል እንዲሆንና የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል።

ተ) የወረዳው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በህብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጁ ያደርጋል። ለተደራጁትም የህብረት ሥራ ማኅበራት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

ቸ) በወረዳው የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች እንዲታውቁና በህብረተሰቡ ተሳትፎ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

ኀ) ህዝቡን ለልማት ሥራዎች በማነሳሳት ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ እንዲሳተፍ ያደርጋል።

ኘ) ስለ ሥራው አፈጻጸም ለወረዳው ም/ቤትና ለዞን አስተዳዳሪ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል።

አ) የወረዳው ዕቅድ ለቀበሌ መስጠት፣ የቀበሌን ዕቅድ በዝርዝር ማየትና አፈፃፀሙን በቅርብ መከታተል።

ከ) በታወቀ ፕሮግራም የሚፈፀም የቀበሌ አመራሮች የልምድ ልውውጥ እንዲኖርና አንዱ ከሌላው እንዲማር ማድረግ፣ ይህም ሕዝቡን በማስተባበር ፤ የልማት ሥራዎችን በመሥራት፤ የሕዝቡን አስተዳደራዊ ችግሮች በመፍታት ዙሪያ መሆን ይኖርበታል።

ኸ) የቀበሌው አመራሮች በሀገሪቷና በክልሉ ጠቃሚ አዋጆች፣ ሕጎችና መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተለያዩ ርእሶች ላይ ሙያተኞችን በማዘጋጀት ማወያየት ይኖርበታል።

ወ) ሕዝቡን በቅንነት የማገልገል አቅማቸው እንዲጠናከርና ሙስናን በፅናት ለመታገል የሚያስችል አቅም እንዲፈጠርላቸው አጫጭር ሴሚናሮችን በሙያተኞች በማዘጋጀት መስጠት፤

ዘ) የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ጉድለቶቹን እየገመገመ በየጊዜው የማስተካከያ እርምጃዎችን ከመውሰድ በተጨማሪ ሁሉም አባላት የኃላፊነትና የተጠያቂነት መንፈሳቸው እንዲዳብር የሥራ አፈፃፀም ብቃታቸው ከፍ እንዲል፣ በወረዳው ውስጥ ባሉ ሙያተኞች አንዳንዴም ከክልሉ እየጋበዙ የእለት ሴሚናሮችን በመስጠት የማጠናከርና የማብቃት ሥራ በዕቅድ ተይዞ መተግበር አለበት።

ዠ) በወረዳው ም/ቤትና በዞን አስተዳዳሪ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

### ክፍል አራት
### የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሥልጣንና ተግባር

፯· የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባራት

የወረደወ ወነ አሰተደደረ ተጠረነተ ለወረዳው ም/ቤትና ለክልሉ ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ በወረዳው የሚከናወኑ፣ በአስተዳደር ም/ቤት የፀደቁና ከበላይ አካላት የሚሰጡትን ተግባራት አጣምሮ ይመራል፤ ይከታተላል፣ ሥራዎችን ያስፈፅማል።

ለ) የወረዳውን አስተዳደር ም/ቤት ያደራጃል፣ ይመራል።

ሐ) የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል መተግበራቸውን ያረጋግጣል።

(d) Miseensoota Mana Maree Bulchiinsa Aanichaa, hojii dhaabbilee adda addaatiifi gandoota isa jalatti argamanii ol'aantummaan ni qindeessa, ni hoggana, ni to'ata.

(e) Karooronniifi sagantaaleen tajaajiltoota hawaasummaa, misooma diinagdee yeroo eeganii qophaa'uu isaanii ni to'ata, hojiirra oluu isaanii ni hordofa.

(f) Humnoota tasgabbiifi polisii seeraafi sirna Aanichaa kabachiisuuf dhaabatan ol'aantummaan ni hoggana, ni to'ata.

(g) Miseensoota Mana Maree Bulchiinsa Aanichaa Mana Maree Aanichaatiif dhiheessee ni muudamsiisa.

(h) Mana Maree Bulchiinsa Aanichaa walgahii ni waama, ni geggeessa. • Walgahichi akkaataa miseensoonni Mana Maree Bulchiinsaa murteessaniin yeroo isaa eeggatee akka adeemsifamu ni godha.

(i) Mana Maree Aanichaatiifi Bulchaa Godinaatiif yeroo yeroodhaan gabaasa ni dhiheessa.

(j) Hojiiwwan biroo, Mana Maree Aanichaafi Bulchaa Godinaatiin kennamaniif ni raawwata.

8. *Aangoo fi hojii Itti Aanaa Bulchaa Aanaa*

Itti Aanaan Bulchaa Aanaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiif ta'ee aangofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:–

(a) Yeroo Dura Taa'aa Bulchaa Aanaa hinjirre bakka bu'ee ni hojjeta.

(b) Hojiiwwan Dura Taa'aa Aanaatiin kennamaniif biroo ni raawwata.

9. *Aangoofi hojii ittigaafatamaa misooma baadiyyaa Aanichaa*

Ittigaafatamaan misooma baadiyyaa Aanichaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi Ittigaafatamaa Waajjira Misooma baadiyyaa Godinaatiif ta'ee aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:-

(a) Waajjira Misooma baadiyyaa Aanichaa ni gurmeessa, ni hoggana.

(b) Imaammataafi tarsiimoowwan misooma baadiyyaa hojiirra oolchuuf adda durummaan ni socho'a.

(c) Sagantaaleen misooma oomishaafi oomishtummaa qonnaan bulaa guddisuuf sadarkaa Naannootti bahan bifa haala qabatamaa Aanichaatiin walsimeen hojiirra ooluusaa ni hordofa. Keessumattuu hojii paakeejii ekisteenshiiniitiif xiyyeefannaa kennee ni socho'a.

(d) Haala calla guddiftoonni misooma ariifachiisaa baadiyyaatiif barbaachisaa ta'an itti argamaniifi yeroo eeganii gara Aanichaa itti dhufaniifi fayyadamaa bira itti gahan ni mijeessa.

(e) Karoora misooma baadiyyaa Aanichaa ni qopheessa, waajjira Bulchiinsa Aanichaatiin erga raggaasise booda hojiirra ni oolcha.

(f) Aanicha keessatti karaa sagantaan wabii nyaataa itti mirkanaa'uufi tarsiimoon hiyyummaa hir'isuu hojiirra itti oolu ni mijjeessa. Sagantaan ummata qubachiisuu fedhiirratti hundaa'e akka adeemsifamu ni godha.

(g) Daandiifi bu'uroonni misoomaa kanneen biroo Aanicha keessatti akka babal'atan ni godha.

(h) Hojiiwwan misooma jallisii akka babal'atanii fi qonnaan bulaa biratti aadaa akka ta'an ni godha.

(i) Sagantaaleen misoomaa fi eegumsa midhaanii, beeyiladaafi qurxummii, fayyaa beeyiladaa fi bunaa cimanii akka adeemsifaman hordoffii barbaachisaa ni godha.

(j) Aanicha hojiiwwan wabii hawaasummaa ol'aantummaan ni hogana, hojiirra ooluusaanii ni to'ata.



መ) የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት አባላት፤ የልዩ ልዩ ተቋሞችንና በሥሩ የሚገኙ ቀበሌሎችን ሥራ በበላይነት፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል።

ሠ) የወረዳው ማኅበራዊ አገልግሎቶች፤ የኢኮኖሚ ልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፤ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል።

ረ) የወረዳውን ሕግና ሥርዓት ለማስከበር የተቋቋሙ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎችን በበላይነት ይቆጣጠራል።

ሰ) የወረዳውን የአስተዳደር ም/ቤት አባላት ለወረዳው ም/ቤት አቅርቦ ያሾማል።

ሸ) የወረዳውን አስተዳደር ም/ቤት ስብሰባ ይጠራል፤ ይመራል። ስብሰባው አስተዳደር ም/ቤት አባላት በሚወስኑት መሠረት ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ያደርጋል።

ቀ) ለወረዳው ም/ቤትና ለዞን አስተዳዳሪ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል።

በ) በወረዳው ም/ቤትና በዞን አስተዳዳሪ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፰· <u>የወረዳ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳው ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ቀይኖሩታል።

ሀ) ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተተክቶ ይሠራል።

ለ) በዋና አስተዳዳሪው ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፱· <u>የወረዳ የገጠር ልማት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳ የገጠር ልማት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የገጠር ልማት ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) የወረዳውን የገጠር ልማት ጽ/ቤት ያደራጃል፤ ይመራል።

ለ) የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በግንባር ቀደምትነት ይንቀሳቀሳል።

ሐ) የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሰደግ በክልል ደረጃ የሚወጡት የልማት ፕሮግራሞች ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል። በተለይም ለኤክስቴንሽን ፓኬጅ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል።

መ) ለፈጣን የገጠር ልማት አስፈላጊ የሆኑት ግብአቶች የሚገኙበትን ሁኔታና ወቅቱን ጠብቀው ወደ ወረዳው የሚመጡበትንና ተጠቃሚው ዘንድ የሚደርሱበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ሠ) የወረዳውን የገጠር ልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፤ የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ካፀደቀ በኋላ ተግባራዊ ያደርጋል።

ረ) በወረዳው ውስጥ የምግብ ዋስት ፕሮግራም የሚረጋገጥበትንና የድኅነት ቅነሳው እስትራቴጂ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ያመቻቻል ። በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሰፈራ ፕሮግራም እንዲካሄድ ያደርጋል ።

ሰ) መንገድንና ሌሎች መሠረተ ልማቶች በወረዳው ውስጥ እንዲስፋፉ ያደርጋል ።

ሸ) የመስኖ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉና በአርሶ አደሩ ዘንድ ባህል እንዲሆኑ ያደርጋል ።

ቀ) የእህል ፣ የቤት እንስሳትና ዓሣ ፣ የከብት ሕክምናና የቡና ጥበቃ የልማት ፕሮግራሞች ተጠናክረው እንዲካሄዱ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል ።

በ) ወረዳውን በማሕበራዊ የሥራ ዋስትና በበላይነት ይመራል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይቆጣጠራል።

(k) Qaamoonni hawaasaa adda addaa rakkoolee hawaasummaatiif saaxilaman hanga danda'ametti deebi'anii akka dhaabbataniifi hawaasa wajjin makamanii tooftaa lammii oomishaa itti ta'an ni qiyasa, hojiirra ni oolcha.

(l) Tooftaa barsiifatoonni adaa miidhaa hordofsiisan keessumattuu butiifi humnaan gudeeduun itti dhabamaniifi fuudhaafi heerumni waljaala namoota walfuudhuu qofarratti kan hundaa'e akka ta'uufi maatiin eeguumsi seeraa maatiif akka godhamu qiyaasee hojiirra akka oolu ni godha.

(m) Eeguumsiifi kunuunsi Naannoo hojiirra akka oolu ni godha.

(n) Aadaan hojii ummataa akka gabbatu tooftaalee adda addaa qiyaasee ni sochoo'a.

(o) Qonnaan bulaan liqii bittaa calla guddiftoota qonnaatiif tahu argachuu isaa ni mirkaneessa. Liqichis yeroon deebi'uusaa ni hordofa.

(p) Oomishoonni qonnaan bulaa qulqullinni isaanii eegamee, gabayaarratti dorgomoo tahuudhaan, qonnaan bultootaaf galii gaarii akka argamsiisan qonnaan bulaan tajaajila teekniikaafi gorsaa argachuu isaa ni hordofa.

(q) Baajanni Mootummaa damichaaf ramadame karaa sirrii ta'een mosooma baadiyyaatiif ooluusaa ni hordofa, ni to'ata.

(r) Hojiiwwan misooma baadiyyaa hunduu Aanicha keesatti jijjiirama fidaa jiraachuu isaanii ni gamaaggama.

(s) Qonnaan bulaan teeknolojii ammayyaa wajjiin akka walbaru leenjiiwwan misooma qonnaa argachaa jiraachuusaa ni hordofa.

(t) Misooma baadiyyaafi qonnaarratti dubartoonni dhiirota wajjiin walqixxee fayyadamtoota ta'uusaanii ni hordofa.

(u) Balaan uumamaafi namaan raawwatamu yeroo qunnamu haala imaammata Qophiifi Ittisa balaa wajjiin walsimeen ummatichi gargaarsa akka argatu ni godha.

(v) Waa'ee raawwannaa hojii isaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi Waajjira Misooma baadiyyaa Godinaatiif gabaasa ni dhiheessa.

(w) Hojiiwwan biroo, Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi Ittigaafatamaa Waajjira Misooma Godinaarraa kennamaniif ni raawwata.

0). *Aangoofi hojii ittigaafatamaa Ijaarsa dandeettii Aanichaa*

Ittigaafatamaan ijaarsa dandeettii Aanichaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi ittigaafatamaa waajjira ijaarsa dandeettii Godinaatiif ta'ee aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:-

(a) Hojiiwwan ijaarsa dandeettii Aanichaa ni karoorsa, ni gurmeessa, ni hoggana, ni qindeessa, ni to'ata.

(b) Tooftaa tarsiimoowwaniifi sagantaaleen ijaarsa dandeettii Aanicha keessatti hojiirra itti oolan ni qiyaasa, hojiirra ni oolcha.

(c) Sagantaan fooyya'insa Siviil Sarviisii manneen hojii Aanichaa keessatti hojiirra akka oolu ni karoorsa, adeemsa raawwii manneen hojii ni hordofa, ni gamaaggama, tarkaanfiin sirreessaa barbaachisaan yeroon akka fudhatamu ni godha.

(d) Hawaasichi mirga tajaajila Mootummaa argachuu akka kabachiifatu, haala dureewwan guutuu qabu akka kabaju, qajeelfamoota naamuusaa kudha lameen hubatee hojiirra akka oolchuufi amala malaammaltummaa waraanuu akka gabbisu waltajjiiwwan hawaasichi walirraa itti baratu ni qopheessa, akka mari'atu ni godha.

ተ) ለማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡትን የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በተቻለ መጠን ተመልሰው እንዲቋቋሙና ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው አምራች ዜጋ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል።

ቸ) ጐጂ ባህላዊ ልምዶች በተለይ ጠለፋና አስገድዶ መድፈር የሚወገዱበትንና ጋብቻ በሁለት ተጋቢዎች መፈቃቀድ ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆን እና ቤተሰብ ሕጋዊ ከለላና ጥበቃ እንዲደረግለት ስልት ቀይሶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

ነ) የሕብረተሰቡ የሥራ ባህል እንዲጐለብት የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ ይንቀሣቀሣል።

ኘ) አርሶ አደሩ ለግብርና ግብአቶች መግዣ የሚሆን ብድር ማግኘቱን ያረጋግጣል ። ብድሩም በወቅቱ መመለሱን ይከታተላል ።

አ) የአርሶ አደሩ ምርቶች ጥራታቸው ተጠብቆ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ በመሆን ለአርሶ አደሩ ጥሩ ገቢ እንዲያስገኙ አርሶ አደሩ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ማግኘቱን ይከታተላል ።

ኀ) የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

ከ) ለዘርፉ የተመደበው የመንግሥት በጀት በተገቢው መንገድ ለገጠር ልማት መዋሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

ኸ) የገጠር ልማት ሥራዎች ሁሉ በወረዳው ውስጥ ለውጥ እያመጡ መሆናቸውን ይገመግማል ።

ወ) አርሶ አደሩ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቅ የግብርና ልማት ሥልጠናዎችን እያገኘ መሆኑን ይከታተላል።

ገ) በገጠርና በግብርና ልማት ላይ ሴቶች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ይከታተላል።

ጠ) የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ አደጋ ሲያጋጥም ከአደጋ መከላከል ፖሊሲ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ሕዝቡ እርዳታ እንዲያገኝ ያደርጋል።

ጨ) ስለ ሥራው አፈፃፀም ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የገጠር ልማት ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

የ) ከወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ከዞን ልማት ጽ/ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲ <u>የወረዳ አቅም ግንባታ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳ አቅም ግንባታ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) የወረዳውን የአቅም ግንባታ ተግባራት ያቅዳል ፤ ያደራጃል፡ ይመራል ፤ ያስተባብራል ፤ ይቆጣጠራል ፡

ለ) የአቅም ግንባታ እስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ ተግባራዊ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል ፡ ተግባራዊ ያደርጋል ።

ሐ) የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በወረዳው መ/ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ያቅዳል ፡ የመ/ቤቶችን የመተግበር ሂደት ይከታተላል ፡ ይገመግማል ፡ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ እንዲወሰድ ያደርጋል ፤

መ) ኅብረተሰቡ የመንግሥት አገልግሎት የማግኘት መብቱን እንዲያስከብር ፡ ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያከብር ፤ አሥራ ሁለቱን የሥነ–ምግባር መርሆዎች ተገንዝቦ ተግባራዊ እንዲያደርግና ሙስናን የመዋጋት ባህርይ እንዲዳብር ኅብረተሰቡ የሚማርበትን መድረኮች ያዘጋጃል ፡ እንዲወያይ ያደርጋል ፡

(e) Imaammanni barnootaa haarawni manneen barnootaatti hojiirra ooluusaa, Bulchiinsaafi misooma manneen barnootaarratti hirmaannaan hawaasichaa guddachuusaa, qulqullinni barnootaa eegamuusaa ni hordofa, ni to'ata.

(f) Tajaajilli eeguumsa fayyaa hawaasichaaf sirriitti kennamuusaa ni hordofa, ni mirkaneessa.

(g) Hawaasni Aanichaa fayyummaansaa eegamee lammii oomishaa akka tahu tooftaa eegumsa fayyaa naannawaafi dhukkuba ittisuu ni qiyaasa, hojiirra ni oolcha.

(h) Fedhii ijaarsa humna raawwachiisummaa manneen hojii raawwachiiftuu Aanichaa ni qorata, karoora ijaarsa dandeettii ni qopheessa, Bulchiinsa Aanaatiifi itti gaafatamaa ijaarsa dandeettii godinaaf ni dhiheessa, yeroo raggaasifamu qaamoota dhimmi ilaalu waajjin qunnamuudhaan ni raawwachiisa.

(i) Waa'ee raawwannaa hojii isaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi itti gaafatamaa ijaarsa dandeettii godinaatiif gabaasa ni dhiheessa.

(j) Hojiiwwan biroo, Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi ittigaafatamaa ijaarsa dandeettii godinaarraa kennamaniif ni raawwata.

11) *Aangoofi hojii itti gaafatamaa Bulchiinsaafi Haqaa Aanichaa*

Ittigaafatamaan Bulchiinsaafi Haqaa Aanichaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi ittigaafatamaa Bulchiinsaafi Haqaa godinaatiif ta'ee aangoo fi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:-

(a) Hojiiwwan Bulchiinsaafi Haqaa Aanichaa ni karoorsa, ni gurmeessa, ni hoggana, ni qindeessa, ni to'ata.

(b) Karooraafi Baajeta waggaa waajjirichaa ni qopheessa, Mana Maree Bulchiinsaatiin yeroo raggaasifamu hojiirra ni oolcha.

(c) Aanichatti ol'aantummaan seeraa akka mirkanaa'u, mirgoonniifi walabummaan Heerummaa lammiiwwanii osoo hin caccabin hojiirra akka oolan ni godha, hawaasichaaf tajaajilli saffisaafi haqummaa kennamuusaa ni mirkaneessa.

(d) Haala haawaasichi mirgoota isaatti fayyadamaa ta'uu fi mirgasaa kabachiifachuu itti danda'u ni mijeessa, haala hubannoon seeraafi hirmaannaa diimokiraatawaan hawwaasichaa itti guddatu ni karoorsa, hojiirra ni oolcha.

(e) Aanichatti nageenyiifi tasgabbiin akka jiraatu ni godha, humnoota milishaafi poolisii ni gurmeessa, ni qindeessa, ni hoggana.

(f) Hojiiwwan Bulchiinsa Gandaalee Aanicha jalatti argamanii ni qindeessa, hojii isaanii sirriitti raawwachuu isaanii ni hordofa.

(g) Iyyannoowwan hawaasicharraa dhihaatan ni qulqulleessa, yeroodhaan deebii akka argatan ni godha.

(h) Karaa dandeettiin qaamota isa jala jiranii itti guddatu ni karoorsa, humnootiin poolisiifi milishaa leenjii gahumsaa sirrii akka argatan ni godha.

(i) Manneen hojii isa jalatti argamanitti imaammatoonni, danboonniifi qajeelfamoonni mootummaa hojiirra ooluusaanii ni mirkaneessa.

(j) Manneen hojii isa jalatti argamanitti sagantaaleen ijaarsa dandeettii, fooyya'insa siviil sarviisii fi haqaa sirriitti hojiirra ooluusaanii ni hordofa, tajaajila malaammaltummaarraa qulqullaa'eefi saffiisaa hawaasichaaf kennuusaanii ni to'ata.



ሠ) አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ በትምህርት ቤቶች ተግባራዊ መሆኑን ፣ በትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ልማት የኅብረተሰቡ ተሳትፎ መጎልበቱን ፣ የትምህርት ጥራት መጠበቁን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል፤

ረ) ለኅብረተሰቡ ተገቢው የጤና አገልግሎት መሰጠቱን ይከታተላል ፤ ያረጋግጣል ፤

ሰ) የወረዳው ኅብረተሰብ ጤንነቱ ተጠብቆ አምራች ዜጋ እንዲሆን የአካባቢ ጤና አጠባበቅና በሽታን የመከላከል ስልት ይቀይሳል ፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፤

ሸ) የወረዳውን አስፈጻሚ መ/ቤቶች የማስፈጸም አቅም ግንባታ ፍላጎቶች ያጠናል ፣ የአቅም ግንባታ ዕቅድ ያዘጋጃል ፣ ለወረዳው አስተዳደሪና ለዞን የአቅም ግንባታ ኃላፊ ያቀርባል ፣ ሲፀድቅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገናኘት ያስፈጽማል።

ቀ) ስለ ሥራው ክንውን ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የአቅም ግንባታ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል።

በ) ከወረዳው ዋና አስተዳዳርና ከዞን የአቅም ግንባታ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፲፩· <u>የወረዳው የአስተዳደርና የፍትህ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳው የአስተዳደርና የፍትህ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞኑ የአስተዳደርና የፍትህ ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

ሀ) የወረዳውን የአስተዳደርና የፍትህ ተግባራት ያቅዳል፤ ያደራጃል ፤ ይመራል ፤ ያስተባብራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

ለ) የጽ/ቤቱን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ፤ በአስተዳደር ም/ቤት ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል ፤

ሐ) በወረዳው የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ፤ የዜጎች ህገ–መንግሥታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፤ ለህብረተሰቡ የተቀላጠፈና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠታቸውን ያረጋግጣል።

መ) ህብረተሰቡ የመብቶቹ ተጠቃሚ የሚሆንበትንና መብቱን ሊያስከብር የሚችልበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤ የህብረተሰቡ የሕግ ግንዛቤና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ የሚያድግበትን ሁኔታ ያቅዳል ፤ ተግባራዊ ያደርጋል ፤

ሠ) በወረዳው ሰላምና ፀጥታ እንዲኖር ያደርጋል ፤ የፖሊስና የሚሊሺያ ኃይሎችን ያደራጃል ፤ ያቀናጃል ፤ ይመራል፤

ረ) በወረዳው ሥር የሚገኙ የቀበሌ አስተዳደር ሥራዎች ያስተባብራል ፤ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል ።

ሰ) ከህብረተሰቡ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ያጣራል ፤ ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል ፤

ሸ) በሥሩ የሚገኙ አካላት አቅም ስለሚጎለብትበት መንገድ ያቅዳል ፤ የፖሊስና የሚሊሺያ ኃይሎች ተገቢውን የብቃት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል ፤

ቀ) በሥሩ በሚገኙ መ/ቤቶች የመንግሥት ፖሊሲዎች ፤ ደንቦችና መመሪያዎች መተግበራቸውን ያረጋግጣል ።

በ) በሥሩ በሚገኙ መ/ቤቶች የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ፤ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ እና የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በትክክል መተግበራቸውን ይከታተላል ፤ ከሙስናና ከአድልኦ የፀዳና ቀልጣፋ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መሰጠታቸውን ይቆጣጠራል ።

(k) Aanaalee Naannoo biroo wajjiin waldaangessanitti walqunnamtiin gaariin akka jiraatuufi ummata Naannichaafi Ummatoota Naannoolee biroo naannawa daangaa jiraatan jidduutti tokkummaafi obboleeyyummaan akka jiraatu ni hojjeta. Wantoonni walitti bu'iinsaaf ka'uumsa ta'an akka dhabaman ni godha. Walitti bu'iinsi yeroo uumamu qaamota dhimmi ilaalu wajjiin ta'uudhaan walitti bu'iinsichi karaa nagayaafi diimokiraasawaatiin akka hiikamu ni godha.

l) Waa'ee raawwannaa hojii isaa gabaasa ni qopheessa, Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaafi ittigaafatamaa Bulchiinsaafi Haqaa godinaatiif ni dhiheessa.

m) Hojiiwwan biroo, Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi ittigaafatamaa Bulchiinsaafi Haqaa godinaarraa kennamaniif ni raawwata.

12. Aangoofi hojii Ittigaafatamaa Gamtaawina Ummataa Aanaa

Itti gaafatamaan Gamtaawina Ummataa Aanichaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi Itti gaafatamaa Waajjira Gamataawina ummataa godinaatiif ta'ee aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:;-

(a) Qaamooleen hawaasaa adda addaa gurmaawanii mirgootaafi bu'aawwan diinagdee, hawaasummaa fi siyaasaa isaanii akka kabachiifatan haalawwan ni mijeessa.

(b) Haala qabatamaa Aanichaarratti hundaa'uudhaan tooftaa waldaaleen hojii gamtaa itti babal'atan ni qiyaasa, hojiirrra akka oolan ni godha.

(c) Oomishoonni waldaalee hojii gamtaa qulqullina qabaatanii gabayaa gaarii argachuudhaan miseensotaan galii gaarii argamsiisuu haalli itti danda'an akka mijaa'u ni godha.

(d) Waldaaleen hojii gamtaa liqii barbaachisaa akka argatan haalawwan ni mijeessa, liqiin kenname akkaataa karoorfameen hojiirra ooluusaafi yeroosaa eegee qaama liqeesseef deebi'uusaa ni mirkaneessa.

(e) Dargaggoonni Aanichaa gurmaawanii jaalala hojii fi naamusa gaariin akka ijaaraman, humna ho'aa isaanii hojii misoomaarra akka oolchan, lammii fayyummaan isaanii eegame akka ta'aniifi akkaataa fedhii isaaniitti sagantaalee galii argamsiisu addaddaa keessatti hammatamuu isaanii ni hordofa.

(f) Dubartoonni Aanichaa mirgoonni isaanii Heera Mootummaa kabajamaa jiraachuufi hirmaannaan diinagdee. hawaasummaafi siyaasaa isaanii guddachaa deemuusaa ni hordofa, ni mirkaneessa.

(g) Waldaaleen ummataa Aanicha keessatti argaman akka cimaniifi roga ijaarsa sirna dimorkiraasiifi misoomaatiin hirmaannaan isaanii akka guddatu ni godha.

(h) Hojii dhabummaafi farroonni guddina hawaasummaa kanneen biroo akka dhabaman haalawwan ni mijeessa.

(i) Iddoowwan oolmayaa ispoortiifi kilaboonni akka babal'atan ni godha.



ተ) ከአዋሣኝ የክልል ወረዳዎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖርና በድንበር አካባቢ በሚኖሩ የክልሉ ሕዝቦችና የሌሎች ክልሎች ሕዝቦች መካከል የአን ድነትና የወንድማማችነት ስሜት እንዲኖር ይሠራል ። ለግጭት መንሥኤ የሚሆኑ ነገሮች እንዲወገዱ ያደርጋል ፤ ግጭት ሲፈጠር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ግጭቱ በሰላማዊና ዴሚክራሲያዊ መንገድ እንዲፈታ ያደርጋል ።

ቸ) ስለ ሥራው ክንውን ሪፖርት ያዘጋጃል ፤ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ እና ለዞን የአስተዳደርና የፍትህ ኃላፊ ያቀርባል ።

ኀ) ከወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ከዞን የአስተዳዳርና ፍትህ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ውናል።

፲፪· <u>የወረዳው የሕዝብ አደረጃጀት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳው የሕዝብ አደረጃጀት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን ሕዝብ አደረጃጀት ጽ/ቤት ሆኖ የሚከ ተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ።

ሀ) የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተደራጅተው ኤኮኖ ሚያዊ ፤ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መብቶቻቸውንና ጥቅሞ ቻቸውን እንዲያስከብሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ።

ለ) በወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመሥረት የህብረት ሥራ ማህበራት የሚስፋፉበትን ዘዴ ይቀይሳል ፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ።

ሐ) የህብረት ሥራ ማህበራት ምርቶች ጥራት ኖሮአቸው ጥሩ ገበያ በማግኘት ለአባላቱ ጥሩ ገቢ ለማስገኘት የሚች ሉበት ሁኔታ እንዲመቻች ያደርጋል ።

መ) የህብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊ ብድር እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፤ የተሰጠው ብድር በታቀደው መሠረት ሥራ ላይ መዋሉንና ብድሩም ወቅቱን ጠብቆ ላበደረው አካል መመለሱን ያረጋግጣል ።

ሠ) የወረዳው ወጣቶች ተደራጅተው በጥሩ የሥራ ፍቅርና ዲሲፕሊን እንዲታነፁ ትኩስ ጉልበታቸውን በልማት ሥራ ላይ እንዲያውሉ ፤ ጤናቸው የተጠበቀ አምራች ዜጋ እንዲሆኑና በዝንባሌአቸው መሠረት በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞች መታቀፋቸውን ይከታተላል ።

ረ) የወረዳው ሴቶች ሕገ–መንግሥታዊ መብቶቻቸው እየተ ከበረና ኢኮኖሚያዊ ፤ ማህበራዊ ፤ ፖለቲካዊ ተሳትፎ አቸው እየጎለበተ መሆኑን ይከታተላል ፤ ያረጋግጣል፡

ሰ) በወረዳው ውስጥ ያሉት የብዙኀን ማህበራት እንዲጠና ከሩና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታውና በልማቱ ረገድ ተሳትፎአቸው እንዲጎለበት ያደርጋል ።

ሸ) ሥራ አጥነትና ፤ ሌሎች የማህበራዊ ዕድገት ጠንቆች እንዲወገዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ።

ቀ) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና ክለቦች እንዲስፋፉ ያደርጋል።

(j) Karooraafi tooftaa dubartoonni Aanichaa gama diinagdeetiin ballinaan gurmaawanii socho'uudhaan diinagdee Naannichaa keessatti gahee murteessaa akka taphataniifi hiyyummaarraa akka bahan dandeessisu qiyaasee hojiirra akka oolu ni godha, hojiirra ooluusaatiis ciminaan ni hordofa.

(k) Aanicha keessatti hojiiwwan wabii hawaasummaa ol'aantummaan ni hoggana, hojiirra ooluusaanii ni to'ata.

(l) Qaamoonni hawaasaa adda addaa rakkoolee hawaasummaaatiif saaxulaman hanga danda'ametti deebi'anii akka dhaabbataniifi hawaasa wajjiin makamanii tooftaa lammii oomishaa itti ta'an ni qiyaasa, hojiirra ni oolcha.

(m) Tooftaa barsiifatoonni aadaa miidhaa hordofsiisan keessumattuu butiifi humnaan gudeeduun itti dhabamaniifi fuudhaafi heerumni waljaalala namoota walfuudhuu qofarratti kan hundaa'e akka ta'uufi maatiin eeguumsi seera maatiif akka godhamu qiyaasee hojiirra akka oolu ni godha.

(n) Dubartoonni Aanicha gurmaawanii mirgoota isaaniitiif akka qabsaawaniifi walqixxummaan saalaa akka mirkanaa'u ni godha.

(o) Aadaan hojii ummaichaa akka gabbatu tooftaa adda addaa qiyyaasee socho'a.

(p) Waa'ee raawwannaa hojii iisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi ittigaafatamaa Waajjira Gamtaawina Ummataa godinaatiif gabaasa ni dhiheessa.

(q) Hojiiwwan biroo, Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi ittigaafatamaa Waajjira Gamtaawina Ummataa godinaarra kennamaniif ni raawwata

13. Aangoofi jojii ittigaafatamaa qunnamtii ummataafi Beeksisaa Aanichaa

Itti gaafatamaan qunnamtii Ummataafi Beeksisaa Aanichaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi itti gaafatamaa waajjira Qunnamtii Ummataafi Beeksisaa godinaatiif ta'ee aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:

(a) Karoora piroppaagaandaa ummata Aanichaa naannoo nageenyaatti, diimokiraasiifi misoomaatti sochoosuuf dandeessisu qopheessee yeroo hayyamamu hojiirra ni oolcha.

(b) Sochiin caasaa mootummaa fi ummata Aanichaa cunfamee bifa ooduutiin Waajjira Qunnamtii Ummataafi Beeksisaa godiinaatiif yookaan midiyaa Naannichaatiif akka ergamu ni godha.

(c) Ummatichi sochii manneen hojii Aanicha keessatti argamanii akka hubatu bu'aaleen argaman eegzibiishiniif karaa adda addaatiin ummataaf akka beeksifaman ni godha.

(d) Iddoowwan seenaafi hambaawwanii Aanicha keessatti argaman eeguumsiifi kunuunsi barbaachisaan akka godhamuuf ni godha. Ummatichis kanarratti hubannoo akka qabaatu ni godha.

(e) Aadaafi Afaan Ummatichaa akka dagaagu Aanicha keessatti gareewwan hawwisoo, tiyaatiraafi hogbarruu akka dhaabbataniif ummaticha bashannansiisaa akka barsiisan ni godha.

(f) Hawwattoonni Tuurizmii Aanicha keessatti argaman akka beekamanifi hojiirra oolan ni godha.



በ) የወረዳው ሴቶች በስፋት ተደራጅተው በመንቀሳቀስ በክልሉ ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱና ከድህነትም እንዲላቀቁ የሚያስችል ዕቅድና ስልት ቀይሶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፡ ተግባራዊ መሆኑንም በጥብቅ ይከታተላል ።

ተ) በወረዳው ውስጥ የማህበራዊ ዋስትና ተግባራትን በበላይነት ይመራል ፡ መተግበራቸውን ይቆጣጠራል ።

ቸ) ለማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡና የሚጋለጡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አቅም በፈቀደ መጠን እንዲቋቋሙና ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው አምራች ዜጋ የሚሆኑበትን ስልቶች ይቀይሳል ፡ ተግባራዊ ያደርጋል።

ኀ) ጐጂ ባህላዊ ልምዶች በተለይም ጠለፋና አስገድዶ መድፈር የሚወገዱበትንና ጋብቻ በሁለት ተጋቢዎች መፈቃቀድ ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆንና የቤተሰብ ሕጋዊ ከለላና ጥበቃ እንዲደረግላቸው ስልት ቀይሶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ።

ነ) የወረዳው ሴቶች ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና የፆታ ዕኩልነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል ።

ኘ) የሕዝቡ የሥራ ባህል እንዲዳብር የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ ይንቀሳቀሳል ።

አ) ስለ ሥራው አፈፃፀም ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የሕዝብ አደረጃጀት ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

ከ) ከወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ከዞን የሕዝብ አደረጃጀት ጽ/ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

፲፫· <u>የወረዳ የሕዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳው የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የሕዝብ ግንኙነት ማስታወቂያ ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ) የወረዳውን ሕዝብ በሠላም ፣ በዴሞክራሲና በልማት ዙሪያ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል የፕሮፖጋንዳ ሥራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል ።

ለ) የወረዳው መንግሥታዊ መዋቅርና የሕዝቡ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ በዜና መልክ ለዞን የሕዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ጽ/ቤት ወይም ለክልሉ ሚዲያ እንዲላክ ያደርጋል።

ሐ) ሕዝቡ በወረዳው የሚገኙትን የአስፈጻሚ መ/ቤቶች እንቅስቃሴ እንዲገነዘብ የተገኙት ውጤቶች በኤግዚቢሽንና በተለያዩ መንገዶች ለሕዝቡ እንዲተዋወቁ ያደርጋል ።

መ) በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ሥፍራዎችና ቅርሳ ቅርሶች አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያደርጋል ። ሕዝቡም በዚህ ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው ያደርጋል ።

ሠ) የሕዝቡ ባህልና ቋንቋ እንዲበለጽግ በወረዳው ውስጥ የኪነ ጥበባት ፣ የቴአትርና የሥነ–ጽሑፍ ክበቦች እንዲቋቋሙና ሕዝቡን እያዝናኑ እንዲያስተምሩ ያደርጋል፤

ረ) በወረዳው ውስጥ የሚገኙት የቱሪስት መስህቦች እንዲታወቁና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ።

(g) Manneen kitaabaa ummataa akka babal'atan ni godha.

(h) Ummanni Aaniichaa imaammatoota, tarsiimoowwaan misoomaa, qajeelfamootaafi danbiiwwan Moootummaa akka beeku ni godha.

(i) Karoora haala yeroo Aanichaafi biyyattiirratti ummaticha mari'achiisuu dandeessisu baasee hojiirra ni oolcha.

(j) Waltajjiilee hojjattoonni Mootummaa Aanichaa keessatti argaman sochii jijjiiramaa Mootummaa sirriitti hubatanii itti amanuudhaan akka sochoo'an gochuuf dandeessisu ni qopheessa.

(k) Qaamolee hawaasa Aanichaa adda addaatiif waltajjii qopheessuudhaan haala qabatamaa Aanichaa wajjiin walqabachiisuu nageenyarratti, diimokiraasiifi misoomarratti akka mari'atan ni godha.

(l) Walga'iilee Mana Maree torban torbaniifi murtiiwwan darban ummanni Aanichaa akka beeku ni godha, ummanni Aanichaan alatti argamus yoo beeke ni fayyada jedhee kan itti amanu meeshaalee tamsaasa oduutiin akka darban ni godha.

(m) Waa'ee raawwannaa hojii isaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiifi ittigaafatamaa Waajjira Qunnamtii Ummataafi Beeksisaa godinaatiif gabaasa ni dhiheessa.

(n) Hojiiwwan biroo, dura Taa'aa Bulchaa aanichaatiifi ittigaafatamaa Waajjira Qunnamtii Ummataafi Beeksisaa godinaarraa kennamaniif ni raawwata.

14. *Aangoofi hojii ittigaafatamaa faayinaansiifi Misooma Diinagdee Aanichaa*

Itti gaafatamaan Faayinaansiif misooma Diinagdee Aanichaa itti waamamnisaa Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi ittigaafatamaa Waajjira Faayinaansiifi Misooma Diinagdee godinaatiif ta'ee aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:

(a) Karoora hojii isaa qopheessee Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiif ni dhiheessa, yeroo ragga'us hojirra ni oolcha.

(b) Manneen hojii Aanicha keessatti argaman seerota, danbootaafi qajeelfamoota Faayinaansii Naannichaa eeganii hojjechuu isaanii ni hordofa, ni to'ata, hoggansa ni kenna.

(c) Tarsiimoowwan misoomaa Naannichaarratti hundaa'uudhaan karoorota misoomaa Aanichatti raawwataman kan yeroo dheeraa, jiddu-galeessaafi yeroo gabaabaa ni qopheessa, yeroo hayyamamus sirriitti hojiirra ooluusaa ni hordofa, akkaataa qopheessuufi dhiheessuu karoorota misoomaafi pirojaktoota irratti deeggersa teekniikaa ni kenna, pirojaktootas ni gamaaggama.

(d) Gaaffii baajeta idileefi kaappitaalaa Manneen hojii Mootummaa Aanichaatiin dhihaatan qorateefi gamaaggamee wixinee gaaffii baajeta waliigalaa Aanichaa qopheessuudhaan yaada wajjin Mana Maree Aanichaatiif ni dhiheessa. Baajeta hayyamames ni bulcha.

(e) To'annaa Bulchiinsa maallaqaafi qabeenya Mootummaa ni hordofa, ni to'ata, Mana Maree Aanichaatiifi Biiroof ni dhiheessa. Seeronni bittaa meeshaa Mootummaa kabajamanii akka raawwataman ni godha.

ሰ) የሕዝብ ቤተመጻሕፍት እንዲስፋፉ ያደርጋል ።

ሸ) የወረዳው ሕዝብ የመንግሥት ፖሊሲዎችን ፣ የልማት እስትራቴጂዎችን መመሪያዎችንና ደንቦችን እንዲያውቅ ያደርጋል ።

ቀ) በወረዳውና በአገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡን ለማወያየት የሚያስችል ዕቅድ አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል ።

በ) በወረዳው የሚገኙት የመንግሥት ሠራተኞች የመንግሥትን የለውጥ እንቅስቃሴ በሚገባ ተረድተው አምነውበት እንዲቀሳቀሱ ለማድረግ የሚያስችል መድረኮች ያዘጋጃል።

ተ) ለወረዳው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሠላም ፣ በዴሞክራሲያና በልማት ዙሪያ ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማያያዝ መድረኮች አዘጋጅቶ እንዲወያዩ ያደርጋል ።

ቸ) የወረዳውን አስተዳደር ም/ቤት ሣምንታዊ ስብሰባዎችና የተላለፉ ውሣኔዎችን ወረዳው ሕዝብ እንዲያውቀው ያደርጋል ፤ ከወረዳው ውጭ ያለውም ሕዝብ ቢያውቀው ይጠቅማል ብሎ የሚያምንበትን በዜና ማሰራጫዎች እንዲተላለፉ ያደርጋል ።

ኀ) ስለሥራው አፈፃፀም ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የሕዝብ ግንኙነት ና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል ።

ነ) ከወረዳ ዋና አስተዳዳሪውና ከዞን የህዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

፲፬· <u>የወረዳ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የወረዳው የፋይናንስና የኤኮኖሚ ልማት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞን የፋይናንስና የኤኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ።

ሀ) የሥራ ዕቅዱን አዘጋጅቶ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ያቀርባል ፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል ።

ለ) በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስ ህጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጠብቀው መሥራታቸውን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ አመራር ይሰጣል ።

ሐ) በክልሉ የልማት እስትራቴጂዎች ላይ በመመርኮዝ በወረዳው የሚከናወነው የረጅም ፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅዶች ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል ፣ የልማት እቅዶችና የፕሮጀክቶች አዘገጃጀትና አቀራረብ ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል ፣ ፕሮጀክቶችንም ይገመግማል ።

መ) በወረዳው የመንግሥት መ/ቤት ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን የመደበኛና የካፒታል በጀት ጥያቄ አጥንቶና መርምሮ የወረዳውን አጠቃላይ የበጀት ጥያቄ ረቂቅ በማዘጋጀት ከአስተያየት ጋር ለወረዳው ም/ቤት ያቀርባል ። የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል ።

ሠ) የመንግሥት ገንዘብ አስተዳደርና ፣ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ቁጥጥርን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ተገቢውን መግለጫ ለወረዳው ም/ቤትና ለቢሮው ያቀርባል ፣ የመንግሥት ዕቃ ግዥ ህጎች ተከብረው እንዲፈፀሙ ያደርጋል ።

(f) Yeroo barbaachisaa ta'ee argamu gaaffiii baajeta dabalataa qopheessee Mana Maree Bulchiinsa Aanichaatiif ni dhiheessa.

(g) Akkaataa seerootaafi danboota gibiraa, taaksiifi galiiwwan adda addaatiin gibirriifi taaksiin akkasumas galiiwwan taaksii hin ta'in Aanichaaf hayyamame akka sassaabamu ni godha. Galiiwwan Mootummaa sirriitti murtaa'uusaanii, yeroodhaan sassaabamusaaniifi herregni isaaniitiis sirriitti qabamuusaa ni to'ata, ni hordofa. Galii Aanichaa cimsuuf maddoonni galii dabalataa qoratamee akka dhihaatu ni godha.

(h) Manneen hojii Mootummaa Aanichaa keessatti akkaataan qabiinsa herrega Mootummaa sirriitti raawwatamuusaa ni to'ata, herregni Mootummaa akka qoratamu ni godha, akka qophaa'u ni godha, gabaasa ni dhiheessa, tarkaanfii sirreessaa barbaachisaa ni fudhata, ni fudhachiisa.

(i) Qabeenyi Mootummaa mana hojii kamiyyuu jalatti hin bulle, yookaan hojiirra hin ooliin, yookaan nama kamiiyyuu yookaan nama qaama seerummaa qabu jalatti hin bulle waajjiricha jalatti akka bulu ni godha.

(j) Odeeffannoowwan qabeenya uumamaa, diinagdeefi hawaasummaa walitti qindaawanii ibsaawwan istaatistiiksii Aancihaa akka qophaawan ni godha.

(k) Hojiiwwan kaartaa, qorannoo Ji'oogiraafiifi sagantaalee dhimma ummataa (population) Aanichaa ilaallatan ni hordofa, ni gamaaggama, akka hojjetaman ni godha.

(l) Galii waggaa Aanichaa ni karoorsa, galichi yeroo kamitti sassaabamuufi galuu akka qabu lafa kaa'a.

(m) Aanichatti karoora baasiiwwan Aanichatti bifa karoorfameen qusannaafi tokko tokkoon saantimaa hojii misoomaarra ooluusaa mirkaneessuu dandeessisu popheessee ni socho'a.

(n) Karoora sochiiwwan Faayinaansii hundumtuu seera Faayinaansii Mootummaa qofaan ta'uusaa mirkaneessu ni popheessa.

(o) Bulchiinsa Faayinaansii Mootummaa, herrega galiifi baasii, sochiiwwan misooma diinagdee, akkaataa eegumsa qabeenya Mootummaa Bulchiinsa baajetaa........kkf Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi ittigaafatamaa waajjira faayinaansiifi misooma diinagdee godinaatiif ji'a ji'aan kurmaana kurmaanaan, wagga waggaan gabaasa ni erga.

(p) Hojiiwwan biroo, Dura Taa'aa Bulchaa Aanaatiifi itti gaafatamaa Waajjira Faayinansiifi Misooma Diinagdee godinaarraa kennamaniif ni raawwata.

15. Aangoo fi hojii qaamolee raawwachiiftuu biroo

Aangoo fi hojiiwwan qaamolee raawwachiiftuu caasaa Aanaa kanneen biroo kan seektaroota isaaniitti tumame akkuma eegametti ta'ee itti waamamni isaanii Mana Maree Bulchiinsa Aanaatiifi akkasumas seektara isaanii itti aanee jiruuf ta'a.

## *KUTAA SHAN*

Waa'ee Walqunnamtii Manni Maree Bulchiinsa Aanaa qaamolee biroo wajjiin qabu:-

16. *Waa'ee walqunnamtii qaamolee abbaa seerummaa wajjin qabu*

Akkaataa Heera Mootummaa Naannoo Oromiyaa keewwata 63(2) irra taa'een qaamni abbaa seerummaa sadarkaa kamittuu argamu qaama Mootummaa kamiyyuurraa, abbaa aangoo yookaan dhiibbaabiroorraa walabaadha. Kuniis abbootiin seeraa seera qofarratti hundaa'anii kan seerri ajaju qofa walabummaa guutuun akka raawwatan dandeessisuufi. Waan ta'eefis abbaan seerummaa walaba. Qaama raawwachiiftuun hin ajajamu. Kun akkuma jirutti ta'ee Manni Maree Bulchiinsa Aancihaa sirna abbaa seerummaa Aanichaa dhiheenyaan deeggeruutu irra jiraata.



ረ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተጨማሪ በጀት ጥያቄ አዘጋጅቶ ለወረዳው መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል።

ሰ) አግባብ ባላቸው የግብር ፣ የታክስና ልዩ ልዩ ገቢዎች፣ ህጎችና ደንቦች መሠረት ለወረዳው የተፈቀደው ግብርና ታክስ እንዲሁም ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች እንዲሰበሰቡ ያደርጋል ። የመንግሥት ገቢዎች በአግባቡ መወሰናቸውን ፣ በወቅቱ መሰብሰባቸውንና ሂሳባቸውም በትክክል መያዙን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል ። የወረዳውን ገቢ ለማጠናከር ተጨማሪ የገቢ ምንጮች ተጠንቶ እንዲቀርብ ያደርጋል ።

ሸ) የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ በወረዳው የመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ በአግባቡ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፣ የመንግሥት ሂሳብ እንዲመረመር ያደርጋል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል ፣ ሪፖርት ያቀርባል፣ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል ፣ ያስወስዳል።

ቀ) በማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት ሥር የማይተዳደር ወይም በሥራ ላይ ያልዋለ ወይም በማናቸውም ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ባለው ሰው ስር የማይተዳደር የመንግሥት ንብረት በጽ/ቤቱ ስር እንዲተዳደር ያደርጋል ።

በ) ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብት የኤኮኖሚና የማኅበራዊ መረጃዎች ተጠናቅረው የወረዳው እስታትስቲክስ መግለጫዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል ።

ተ) ወረዳውን የሚመለከቱ የካርታ ሥራዎች ፣ የጂኦግራፊ ጥናቶችና የፖፑሌሽን ፕሮግራሞች ይከታተላል ፣ ይገመግማል ፣ እንዲሠሩ ያደርጋል ።

ቸ) የወረዳው ዓመታዊ ገቢ ያቅዳል ፣ ገቢው በምን ወቅት መሰብሰብና መግባት እንዳለበት ያስቀምጣል።

ነ) በወረዳው ወጪዎች በታቀደ መልኩ በቁጠባና እያንዳንዱ ሣንቲም በልማት ተግባር ላይ መዋሏን ለማረጋገጥ የሚያስችል እቅድ አዘጋጅቶ ይንቀሳቀሳል ።

ኘ) ሁሉም የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በመንግሥት የፋይናንስ ህግ ብቻ መሆኑን የሚያረጋግጥ እቅድ ያዘጋጃል ።

አ) የወረዳውን የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ፣ የገቢና የወጪ ሂሳብ ፣ የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴዎች ፣ የመንግሥት ሀብት አጠባበቅ ፣ የበጀት አስተዳደር ወዘተ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለዞኑ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በየወሩ ፣ በየሩብ ዓመቱ ፣ በየዓመቱ ፣ ሪፖርት ይልካል ።

ከ) ከወረዳ ዋና አስተዳዳሪና ከዞን የፋይናንስና የኤኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ተጠሪ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ።

፲፭· <u>የሌሎች አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር</u>

ሌሎች በወረዳ የተዋቀሩ የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራቸው በየሴክተር መሥሪያ ቤታቸው የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነታቸው ለወረዳ አስተዳደር ም/ቤትና እንዲሁም ቀጥሎ ላለው ለራሳቸውም ሴክተር ይሆናል ።

## <u>ክፍል አምስት</u>

የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ከሌሎች አካላት ጋር ስላላቸው ግንኙነት ፣

፲፮· <u>ከዳኝነት አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት</u>

በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ ፷፫(፪) በሰፈረው መሠረት በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግሥት አካል ፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅእኖ ነፃ ነው ። ይህም ዳኞች ህግን ብቻ ተመርኩዘው ህጉ የሚያዘውን ብቻ በሙሉ ነፃነት እንዲያከናውኑ ለማስቻል ነው ። በመሆኑም ዳኝነት ነፃ ነው ። በአስፈፃሚው አካል አይታዘዝም። ይህ እንዳለ ሆኖ የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት የወረዳውን የዳኝነት ሥርዓት በቅርብ መደገፍ ይኖርበታል ።

17. *Waa'ee walqunnamtii Manneen Maree etidiroaa Bulchiinsa Naannoofi Godinaa akkasumas waajjiraaleef qindeessaa wajjin qabu*

(a) Dura Taa'aa Bulchaan Aanichaa itti waamamnisaa Mana Maree Aanichaatiifi Pireezidaantii Mana Maree Bulchiinsa Naannootiifi. Akkaataa Heera Mootummaatiin taa'een Manni Maree Bulchiinsa godinaa itti waamamnisaa Mana Maree Bulchiinsa Naannootiif yoo ta'u Dura Taa'aan Bulchaa godinaa ammoo bakka bu'aa pireezidaantii Buulchiinsa Naannoo ta'eeti hojjeta.

(b) Dura Taa'aan Bulchaa Aanichaa karoora Aanichaa Bulchiinsa godinaatiif ni beeksisa. Gabaasa gamaaggama hojii ji'a sadiifi waggaa Bulchiinsa godinaatiif barreeffamaan ni dhiheessa. Bulchiinsi godinaa gabaasicharratti hundaa'uudhaan deeggersa qabatamaa ni godha.

(c) Waajjiraalee Qindeessaan Aanichaa gabaasa raawwannaa hojii Mana Maree Bulchiinsa Aanichaatiif Dura Taa'aa Bulchaa Aanichaatiif dhiheessan Qajeelchotaafi Deeskiiwwan isaanii godinarra jiraaniif ni dhiheessu. Misoomni baadiyaa Aanaa, Misooma baadiyyaa godinaatiif, kkf.

(d) Manni Maree Bulchiinsa Godinaafi Qajeelchonni akkasumas Deeskiiwwan Qindeessa godinaa walii wajjinis ta'e kopha kophaatti Aanaalee godinatti waamuudhaan yookaan gara Aanaaletti socho'uudhaan gamaaggamaafi to'annoo godhuudhaan deeggersa ni godhu.

(e) Manneen hojiifi waajjiraaleen Aanaa waajjiraalee qindeessaa isaanii Aanichatti argamaniifi deeskiiwwaniifi waajjiraalee isaanii godinaatiif itti waamama ni qabaatu.

18. *Waa'ee walqunnamtii caasaa Bulchiinsa Aanichaa wajjin jiru*

(a) Manni Maree Aanichaa Manni Maree Gandaa karoora waliigalaa Aanichaarratti tartiibaan akka mari'atuufi akka beeku ni godha. Bifa Bulchiinsi gandaa karooricha keessa gahee isaa fudhachuu dandeessisuun oriyenteeshinii ni kenna. Xiyyeeffannaa ol'aanaa Aanichaas akka beeku ni godha.

(b) Waajjiraalee qindeessaan Aanichaa karoora mata mataa isaanii baafatanii Mana Maree Bulchiinsaatiin erga raggaasisan booda sadarkaa gandaatti damee damee hojii isaaniitiin karooricharratti walfalmaniifi amananii gahe gahee isaanii fudhachuu qabu.

(c) Karoora Aanaatti ragga'ee Gandaafi gadi bu'u Manni Maree Gandaa akka beekuufi karoora ganda isaa yeroo raggaasisu karoora Aanichaa wajjiin walqabsiisee akka hubatu gochuun barbaachisaadha.

(d) Hojimaatni karoora Gandichaa waliiwajjiniifi kophaatti fudhachuudhaan tartiibaan ilaaluufi akkaataa karoora baasuurratti deeggersa qabatamaa kennuu jiraachuutu irra jiraata.

(e) Hojimaatni Manni Maree Bulchiinsa Gandaa damee dameedhaaniifi waliiwajjiin gabaasa raawwannaa karoora isaanii itti dhiheeffataniifi raawwannaan isaanii tartiibaan itti gamaaggamamu jiraachuutu irra jiraata.

*BOQONNAA LAMA*
*KUTAA TOKKO*

19. *Akkaataa Filannoofi Muudama miseensota Mana Maree Bulchiinsa Gandaa*

1) Dura Taa'aa Bulchaa Gandaa Miseensota Mana Maree Gandichaa jidduu Dhaaba siyaasa sagalee caalmaya argateen dhihaatee Mana Maree Gandaatiin ni moggaafama.



፲፯· ከክልል መስተዳድርና ከዞን አስተዳደር ም/ቤቶች እንዲሁም ከዞን አስተባባሪ ጽ/ቤቶች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ፣

ሀ) የወረዳው አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳው ም/ቤትና ለክልሉ ፕሬዚዳንት ነው ። በህገ መንግሥቱ ላይ በተቀመጠው መሠረት የዞን አስተዳደር ተጠሪነቱ ለክልል መስተዳድር ም/ቤትና ለፕሬዚዳንቱ ሲሆን የዞን ዋና አስተዳዳሪው ደግሞ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ በዞኑ የፕሬዚዳንቱ ወኪልና የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ ነው ።

ለ) የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የወረዳውን እቅድ ለዞን አስተዳደር ያሳውቃል ። የወረዳውን የሦስት ወርና የዓመት የአስተዳደር ም/ቤት ሥራ ግምገማ ሪፖርት ለዞን አስተዳደር በፅሁፍ ያቀርባል ። የዞኑ አስተዳደር በሪፖርቱ ላይ በመመሥረት ተጨባጭ እገዛ ያደርጋል ።

ሐ) የወረዳው አስተባባሪ ጽ/ቤቶች ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤትና ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የሚያቀርቡትን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በዞን ላለው ተጓዳኝ መምሪያዎችና ዴስኮች ያቀርባሉ ። የወረዳ የገጠር ልማት ለዞን የገጠር ልማት ወዘተ·

መ) የዞን አስተዳደር ም/ቤትና የዞን አስተባባሪ መምሪያዎች እንዲሁም ዴስኮች በጋራ ይሁን በተናጠል ወረዳዎችን ወደ ዞን ጠርተው ወይም ወደ ወረዳዎች ተንቀሳቅሰው ግምገማና ቁጥጥር በማድረግ እገዛ ያደርጋሉ ።

ሠ) የወረዳ መ/ቤቶችና ጽ/ቤቶች በወረዳው ለሚገኙት አስተባባሪ ጽ/ቤቶቻቸውና ለዞን ዴስኮቻቸው ጽ/ቤቶቻቸው ተጠሪነት ይኖራቸዋል ።

፲፰· ከቀበሌው አስተዳደር መዋቅር ጋር ስላለው ግንኙነት

ሀ) የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት የቀበሌው አስተዳደር ም/ቤት የወረዳውን አጠቃላይ እቅድ በዝርዝር እንዲወያይበትና እንዲያውቀው ያደርጋል። የቀበሌው አስተዳደር ከእቅዱ ውስጥ የራሱን ድርሻ ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ኦርየንቴሽን ይሰጣል። የወረዳውን ዋነኛ ትኩረትም እንዲያውቅ ያደርጋል።

ለ) የወረዳው አስተባባሪ ጽ/ቤቶች የየራሳቸውን እቅድ አውጥተው አስተዳደር ምክር ቤት ካስጸደቁ በኋላ በቀበሌ ደረጃ በየሥራ ዘርፋቸው በዕቅዱ ላይ ተከራክረውና አምነው የየድርሻቸውን መውሰድ አለባቸው።

ሐ) በወረዳ ጸድቆ ለቀበሌው የሚወርደውን ዕቅድ የቀበሌው ም/ቤት እንዲያውቀውና የራሱን ቀበሌ ዕቅድ ሲያፀድቅ ከወረዳው እቅድ ጋር አያይዞ እንዲገነዘበው ማድረግ ይገባል።

መ) የቀበሌውን ዕቅድ በጋራና በተናጠል ተቀብሎ በዝርዝር የማየትና በዕቅዱ አወጣጥ ላይ ተጨባጭ ድጋፍ የመስጠት አሠራር መኖር ይኖርበታል።

ሠ) የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት በየዘርፉና በጋራ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን የሚያቀርቡበትና ክንውናቸው በዝርዝር የሚገመገምበት አሠራር መኖር ይኖርበታል።

ምዕራፍ ሁለት
ክፍል አንድ

፲፱· የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት አባላት አመራረጥና አሿሿም

፩· የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ከቀበሌው ም/ቤት አባላት መካከል አብላጫ ድምፅ ባገኘው ድርጅት አቅራቢነት በቀበሌው ም/ቤት ይሰየማል።

2) Muudamni miseensoota Mana Maree Bulchiinsa Gandaa Dura Taa'aa Bulchaa Gandaatiin dhihaatee Mana Maree Gandichaatiin ni raawwatama.

3) Ramaddiin iddoo ittigaafatamummaa miseensotaa hanga danda'ametti damee ogummaa miseensotaa wajjin kan walqabate akka ta'u godhamuu qaba.

4) Miseensonni Mana Maree Bulchiinsa Gandaa shan yoo ta'an, isaannis;
   (a) Dura Taa'aa Bulchaa Gandaa
   (b) Itti aanaa bulchaafi ittigaafatamaa dhimma Qunnamtii Ummataafi Beeksisaa Gandaa
   (c) Ittigaafatamaa Dhimma Gurmaawina Ummataa Gandaa
   (d) Ittigaafatamaa Dhimma Haqaafi Seeraa Gandaa
   (e) Ittigaafatamaa Dhimma Hawaasummaafi Diinagdee Gandaa

*KUTAA LAMA*

20. *Aangoofi Hojii Mana Maree Bulchiinsa Gandaa*

Manni Maree Bulchiinsa Gandaa itti waamamnisaa Mana Maree Gandaatiifi Mana Maree Bulchiinsa Gandaatiif ta'ee Aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:-

(a) Karoorotaafi sagantaalee misoomaa Gandichaa ni qopheessa, Mana Maree Gandaatiif dhiheessee ni raggaasisa, yeroo hayyamamus hojiirra ni oolcha.

(b) Eegumsi, Kunuunsiifi misoomni qabeenya uumamaa akka adeemsifamu ni godha. Ummatichas hojii misoomaatiif ni kakaasa, ni qindeessa.

(c) Nageenyiifi tasgabbiin Gandichaa akka kabajamu ni godha.

(d) Hambaawwan naannawichatti argamaniif eegumsaafi kunuunsa sirrii ni godha, karaa bu'aarra itti oolaniis qaama dhimmi ilaaluuf ni beeksisa.

(e) Aadaafi Afaan Ummatichaa akka dagaagu ni godha.

(f) Iddoowwan oolmaya Ispoortiifi sochiin Ispoortii akka babal'atu ni godha.

(g) Qaammooleen hawaasaa adda addaa waldaalee Hojii Gamtaatiin akka gurmaawan ni godha.

(h) Hawwattoonni Tuuristii Gandichatti argaman akka beekamaniifi bu'aarra akka oolan ni godha.

(i) Waltajjiilee adda addaa qopheessuudhaan ummatichi haalaawwan yeroorratti akka mari'atu ni godha.

(j) Dubartoonni Gandichaa mirgoonni Heerummaa isaanii kabajamuu isaa ni mirkaneessa, dubartoonni sagantaalee galii argamsiisuu adda addaa keessatti akka hammataman haala ni mijeessa.

(k) Waa'ee raawwannaa hojii isaa Mana Maree Gandaatiifi Mana Maree Bulchiinsa Aanaatiif gabaasa ni dhiheessa.

(l) Hojiiwwan Mana Maree Gandaatiifi Mana Maree Bulchiinsa Aanaatiin keennamaniif biroo ni raawwata.

Manni Maree Bulchiinsa Gandaa aangoofi hojiiwwan olitti eeraman bahuuf akkaataa gurmaawina Mana Maree Bulchiinsaatiin taa'een hojiiwwan Mootummaa Gandicha keessatti raawwataman hunda ni hordofa, ni raawwachiisa.

*KUTAA SADII*

*Aangoofi hojiiwwan Miseensota Mana Maree Bulchiinsa Gandaa*

21. *Aangoofi hojii Dura Taa'aa Bulchaa Ganda*

Dura Taa'aan Bulchaa Gandaa itti waamamniisaa Mana Maree Gandichaatiifi Dura Taa'aa Bulchaa anaatiif ta'ee aangoofi hojiiwwan kanatti aanan ni qabaata:-



፪· የቀበሌው አስተዳደር ም/ቤት አባላት ሹመት በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ አቅራቢነት በቀበሌው ም/ቤት ይከናወናል።

፫· የአባላት የኃላፊነት ቦታ ምደባ በተቻለ መጠን ከአባላቱ የሙያ ዘርፍ ጋር የተያያዘ እንዲሆን መደረግ አለበት።

፬· የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት አባላት አምስት ሲሆኑ እነርሱም፡–
   ሀ) የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ
   ለ) የቀበሌው ም/አስተዳዳሪና የሕዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ጉዳይ ኃላፊ
   ሐ) የቀበሌው የሕዝብ አደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ
   መ) የቀበሌው የፀጥታና የፍትህ ጉዳይ ኃላፊ
   ሠ) የቀበሌው የማህበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳይ ኃላፊ

<u>ክፍል ሁለት</u>

፳· የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው ም/ቤትና ለወረዳው አስተዳደር ም/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

ሀ) የቀበሌውን የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ይነድፋል ፤ ለቀበሌው ም/ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

ለ) የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ፤ እንክብካቤና ልማት እንዲካሄድ ያደርጋል ፤ ሕዝቡንም ለልማት ሥራ ያነሳሳል ፤ ያስተባብራል ።

ሐ) የቀበሌው ሰላምና ፀጥታ እንዲከበር ያደርጋል ።

መ) በአካባቢው ለሚገኙ ቅርሳቅርሶች ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል ፤ ጥቅም ላይ ስለሚውሉበትም መንገድ አግባብ ላለው አካል ያሳውቃል።

ሠ) የሕዝቡ ባህልና ቋንቋ እንዲበለጽግ ያደርጋል።

ረ) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲስፋፋ ያደርጋል።

